# *የአቶ ስዬ አብርሃ ወንድም አቶ አሰፋ አብርሃ ከእስር ተፈቱ*

*አቶ አሰፋ አብርሃ ከስምንት አመታት እስር በኋላ ትላንት ማምሻውን ተለቀቁ፡፡ የቀድሞ የህውሀት አባልና የሽግግር መንግስቱ መከላከያ ሚንስትር የነበሩት የአቶ ስዬ አብረሃ መንድም የሆኑት አቶ አሰፋ አብርሃ በሙስና ወንጀል ተከሰው የዘጠኝ አመት እስር ተፈርዶባቸው እንደነበር ይታወሳል፡፡*

*በነአቶ ስዬ የወንጀል ክስ ተጠርጥረው የተያዙ ግለሰቦች ለስድስት አመታት በወህኒ ሆነው ክሳቸውን ሲከታተሉ ቆይተው ከስድስት አመት በኋላ በተሰጠ ውሳኔ ከስድስት አመት በላይ በሚሆን ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኖባቸው ነበር፡፡ ከተከሳሾቹ መሀከል አቶ ስዬና ሁለት ወንድሞቻቸው ከስድስት እስከ ዘጠኝ አመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው እንደነበር አይዘነጋም፡፡*

*አቶ አሰፋ አብረሃ ዘጠኝ አመት ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው የነበረ ሲሆን የአመክሮ ጊዜ ታስቦላቸው ከዛሬ አመት በፊት ከወንድሞቻቸው ጋር መለቀቅ ይገባቸው ነበር፡፡ ማረሚያቤቱ በምን አግባብ አመክሯቸውን እንደከለከላቸው እስካሁን ለመግለፅ ፍቃደኛ ባይሆንም ያገደውን የአመክሮ ጊዜ በመፍቀድ ትላንት ማምሻውን ከእስር እንዲወጡ ፈቅዶላቸዋል፡፡*

*አቶ አሰፋ አብርሃ በጊዜው የመንግሥት ልማት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይባል የነበረን መሥሪያ ቤት በሚንስትር ማዕረግ ይመሩ በነበረበት ወቅት ሙስና ፈፅመዋል ተብለው ለእስር መብቃታቸው ይታወሳል፡፡ ከተከሰሱበት የውንጀል ድርጊት መሀከልም የእቴጌ ጣይቱ ሆቴልን እና ጉለሌ ሳሙና ፋብሪካን ወደ ግል ይዞታነት ለማዘዋወር የተደረገውን ሂደት በሥልጣናቸው በመመካት በዝቅተኛ ዋጋ እንዲሸጥ አድርገዋል፣ ዘመድ አዝማዳቸውን ጠቅመዋል የሚለው ይገኝበታል፡፡ ጣይቱ ሆቴልን ፍፁም ዘአስገዶም ለተባሉ የእህታቸው ባለቤት እንደሸጡት የክስ መዝገባቸው ያስረዳል፡፡*

*አቶ አሰፋ አብረሃ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይከታተሉ የነበሩትን ትምህርት አጠናቀው እንደተመረቁ ደርግ በቁጥጥር ስር አውሏቸው ለዘጠኝ አመታት አስሯቸው የነበረ ሲሆን በ1983 ኢህአዴግ ሀገሪቱን ሲቆጣጠር ነበር ነፃ የወጡት፡፡ ለሥልጣን ያበቃቸው ኢህአዴግም ከህውሀት መሰንጠቅ በኋላ በሳቸውና በሁለት ወንድሞቻቸው ላይ በሙስና ወንጀል ከሷቸው ለሰባት አመታት በእስር እንዲቆዩ ካደረጋቸው በኋላ ትላንት ማምሻውን ነፃ ለመውጣትና ከቤተሰቦቻቸው ለመቀላቀል በቅተዋል፡፡*